የወ/መ/ቁጥር 163277

የልደታ ምድብ 5 ኛ ወንጀል ችሎት

ሐምሌ 06 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኛ ውበቱ አሰፋ

ከሳሽ፡ የፌደራል ዐ/ሕግ - አቶ መሳይ ተድላ ቀረበ

ተከሳሽ፡ 1 ኛ አቶ ነስሩ በሽር ጁሀር - ቀረቡ

2 ኛ ወ/ሮ ፈትያ አረቦ ያሲን - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጠ።

<u>ፍርድ</u>

ዐ/ሕግ ታህሳስ 19 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የወንጀል ክስ አቤቱታ ተከሳሾች በ1996 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ሕግ አንቀፅ 32(1)(ሀ) እና 613(2) ላይ የተደነገገውን በመተላለፍ ግብረአበር በመሆን የሌላ ሰውን ክብር ወይም መልካም ስም ለመጉዳት በማሰብ ሐምሌ 02 ቀን 2001 ዓ.ም ከቀኑ 6፡00 ሰዓት ሲሆን በልደታ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 01/18 ክልል ልዩ ቦታው ሀይሉ ጫካ ተብሎ ከሚጠራው አካባቢ ካለው መስጊድ ግቢ ውስጥ የግል ተበዳይ ሸህ አህመድ ኢብራሂም የተባሉትን ካለምንም ምክንያት አንደኛ ተከሳሽ አንተ ጠንቋይ በማለት ሲናገር፤ ሁለተኛ ተከሳሽ ደግሞ በዚሁ ቀን የግል ተበዳይ ገዝተው ልጃቸው ሊያርድ ያዘጋጀውን በግ ለጥንቆላ ነው የሚያርደው በማለት በመናገራቸው ሁለቱም ተከሳሾች በፈፀሙት ስም ማጥፋት ወንጀል ተከሰዋል በማለት ያቀረበ ሲሆን የዐ/ሕግ የክስ አቤቱታ ለተከሳሾች ደርሷቸውና ተነቦላቸው ከተረዱት በኋላ ክሱን ሳይቃወሙ፤ ድርጊቱን አልፈፀምንም ብለው ክደው በመከራከራቸው ዐ/ሕግ የግል ተበዳይን ጨምሮ ሦስት ምስክሮችን ጨምሮ አቀርቦ ያሰማ ሲሆን የተሰሙት ምስክሮችም እንደ ዐ/ሕግ የክስ አቀራረብና የግል ተበዳይን ስም የሚያጠፋ ንግግር እንደተናገሩ አስረድተዋል። በዚህም መሰረት ተከሳሾች በተከሰሱበት በወንጀል ሕግ አንቀፅ 613(2) ስር እንዲከላከሉ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 142(1) መሰረት ተነግሯቸው እናቀርባለን ብለው ከሄዱ በኋላ ለማቅረብ እንደማይችሉ ገልፀዋል። ከዚህ ለመገንዘብ የሚቻለው ተከሳሾች በዐ/ሕግ በኩል የቀረበባቸውን ክስና ማስረጃ ለማስተባበል የማይችሉ መሆኑን ስለሆነ ተከሳሾችን በወንጀል ሕግ አንቀፅ 613(2) ስር ጥፋተኛ ነው በማለት በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 149(1) መሰረት ውሳኔ ተሰጥቷል።

<u>የቅጣት አስተያየት</u>

<u>ዐ/ሕግ፡</u> ፍ/ቤቱ ደረጃውን ሲወስን ተከሳሾች ዕድሜያቸው ትልቅ በሆነውና
የሐይማኖት አባት በሆኑት የግል ተበዳይ ላይ ስለፈፀሙት ከባድ ተጠሎ
ይወሰን፤ በተጨማሪም ተከሳሾች በጋራ የወንጀል ደርጊቱን የፈፀሙ ስለሆነ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 84(1)(መ) መሰረት ቅጣቱ ከብዶ እንዲወሰን በማለት አመለከተ።
<u>ተከሳሽ፡ 1ኛ ተከሳሽ፡</u> ዕድሜዬ 44 ዓመት ነው፤ ሥራዬ መስጊድ ውስጥ
ማስተማር እና የመስጊዱን አጠቃላይ ንብረት መጠበቅ ነው፤ በወር ብር 300.00(ሦስት መቶ ብርፈ) ገቢ አገኛለሁ፤ የትምህርት ደረጃዬም 12ኛ ክፍል ነው፤ ሰባት ልጆች ያሉኝ ሲሆን አራቱ ለአካለመጠን ያልደረሱ ናቸው አሉ።
<u>2ኛ ተከሳሽ፡</u> ዕድሜዬ 30 ዓመት ነው፤ 1ኛ ተከሳሽ ባለቤቴ ነው፤ ትምህርት አልተማርኩም፤ ሥራም የለኝም፤ የቤት እመቤት ነኝ በማለት አመለከተች።
ፍ/ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ የሚከተለውን ቅጣት ወስኗል።

<u>ውሳኔ</u>

በወንጀል አድራጊ ላይ የሚወሰነው ቅጣት ወንጀል ሕጉን ግብና ዓላማ በሚያሳካ መልኩ ሊሆን እንደሚገባ የታመነ ነው። በዚህም መሰረት የወንጀል ሕግ ዓላማ ለጠቅላላው ጥቅም ሲባል የአገሪቱን መንግስት፤ የነዋሪዎቿን ሰላም፤ ደህንነት፤ ሥርዓት፤ መብትና ጥቅም መጠበቅና ማረጋገጥ ነው።

የወንጀል ሕግ ግብ ደግሞ በዋናነት ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ወንጀል እንዳይፈፀም መከላከል ሲሆን፤ ሕጉን ተላልፈው ወንጀል የሚፈፅሙትን ደግሞ ተቀጥተው ሌሎች ወንጀል እንዳይፈፅሙ፤ እንዲቆጠቡና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ ወይም ተጨማሪ ወንጀሎች እንዳይፈፀሙ እርምጃዎች እንዲወሰድባቸው ማድረግ ስለመሆኑ በ1996 ዓ.ም ከወጣው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ.የወንጀል ሕግ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ለመገንዘብ ይቻላል።

የወንጀል ሕጉን ግብና ዓላማ ለማሳካት ፍ/ቤቱ በወንጀለኛው ላይ የሚወስነው ቅጣት በአንድ በኩል ወጥነትን፤ ተመዛዛኝነትን እና ፍትሀዊነትን ለማረጋገጥ በሌላ በኩል ደግሞ የወንጀል አድራጊውን ግላዊ ባህሪና የወንጀል አፈፃፀም ክብደት መዝኖ ቅጣት ለመወሰን እንዲያስችል ታስቦ የወጣውን የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 እና የወንጀል ሕጉን ድንጋጌዎች መሰረት ተደርጎ የሚከተለው ቅጣት ተወስኗል።

ተከሳሾች ጥፋተኛ የተባሉበት በ1996 ዓ.ም የወጣው የወንጀል ሕግ አንቀፅ 613(2)/የሐሰት ሐሜት ወንጀል ገና ደረጃ ያልወጣለት በመሆኑ የወንጀል ደረጃ እና እርከን የሚወሰነው በቅጣት አወሳሰን መመሪያው አንቀፅ 13 መሰረት ነው። የደረጃ አወሳሰኑም ማክበጃውና ማቅለያው ታሳቢ ከመደረጉ በፊት በወንጀሉ ክብደትና አፈፃፀም መሰረት እንደሚወሰን

መመሪያው በደነገገው መሰረት ደረጃው በሦስት ደረጃዎች ሀ. ዝቅተኛ፤ ለ. መካከለኛ እና ሐ. ከባድ ደረጃ በማለት ይለያል።

ፍ/ቤቱም በወንጀሉ ክብደትና አፈፃፀም መሰረት የወንጀሉን ደረጃ ለመወሰን አፈፃፀሙ ሲታይ የተለየ ከባድ የሚያደርገው ነገር ስልላተገኘ የወንጀል ደረጃው ዝቅተኛ ነው ተብሎ ተወስኗል።

በወጣው ደረጃ መሰረት እርከን ለመወሰን በሕጉ አንቀፅ 613(2) ለወንጀሉ የተቀመጠው ቅጣት ዝቅተኛ ደረጃ ለሆነው ከአንድ ወር እስከ ዘጠኝ ወር ቀላል እስራት ሲሆን መነሻ ቅጣት ደግሞ አምስት ወር ቀላል እስራት ተብሎ የተወሰነ ሲሆን ይህ ደግሞ በአባሪ 1 ላይ በእርከን 4 ላይ የተመለከተ ሲሆን ፍቅድ ስልጣኑም ከአራት ወር እስከ ሰባት ወር በሚደርስ እስራት ነው። የግንዘብ መቀጫውን በተመለከተ ተከሳሾች ጥፋተኛ የተባሉበት የወንጀል ሕግ አንቀፅ 613(2) የወንጀሉ ደረጃ ዝቅተኛ ስለተባለ በቅጣት አወሳሰን መመሪያው አንቀፅ 13(10) መሰረት ከብር አስር እስከ ብር ሦስት ሺህ ሦስት መቶ ብር ባለው ፍቅድ ስልጣን መሰረት ፍ/ቤቱ ቅጣቱን የሚወስን በመሆኑ ከተከሳሾች የገቢ ምንጭ ዝቅተኝነት አንፃር እያንዳንዳቸው በብር 200.00(ሁለት መቶ ብር) መቀጮ እንዲቀጡ ተወስኗል።

ከዚህ በመነሳት የግራቀኙን የቅጣት አስተያየት አመዛዝኖ ለመወሰን ዐ/ሕግ በተጠየቀው መሰረት በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 84(1) (መ) መሰረት ጠቅላላ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት ስለሆነ ፍ/ቤቱ ከላይ የተመለከተውን እርከን በአንድ ከፍ ሲያደርገው እርከኑ ወደ 5 ከፍ ይላል።

ተከሳሾችም የቅጣት አስተያየት እንዲያቀርቡ ተጠይቀው በወንጀል ሕግ አንቀፅ 82 እና 86 መሰረት በማስረጃ የተደገፈ ያላቀረቡ በመሆኑ የቅጣቱን እርከን ፍ/ቤቱ ዝቅ አላደረውም።

ስለሆነም ከላይ እንደተገለፀው ቅጣቱ በአባሪ 1 እርከን 5 ላይ የተመለከተው ፍቅድ ስልጣን/range/ ከስድስት ወር እስከ ዘጠኝ ወር ስለሆነ እያንዳንዳቸው ተከሳሾች ከፈፀሙት የወንጀል ድርጊት አንፃር በሰባት ወር እስራት እንዲቀጡ ተወስኗል።

<u>ትዕዛዝ</u>

1 ኛ. ተከሳሾቹ የሰባት ልጆች ወላጅ እና አስተዳዳሪ በመሆናቸው፤ ሁለቱም ተከሳሾች መታሰራቸው በልጆች አስተዳደግ ላይ መሰረታዊ ችግር የሚያስከትል መሆኑን ከግምት ውስጥ በማስገባት በሁለተኛ ተከሳሽ ላይ የተወሰነው የእስራት ቅጣት ከሚፈፀም ይልቅ አንድ ፅኑ ማስጠንቀቂያ ብቻ ሰጥቶ የወደፊት ፀባይና አመልን ማየቱ በቂ ነው ብሎ ፍ/ቤቱ ስለገመተ የእስራት ቅጣቱን በወንጀል ሕግ አንቀፅ 192 መሰረት በሁለት ዓመት ገደብ ታግዷል።

3 ኛ. ሁለተኛ ተከሳሽ ለመልካም ፀባይ አመራር ዋስትና ይሆናቸው ዘነድ

እያንዳንዳቸው ለብር 100.00(አንድ መቶ ብር) የሚበቃ ዋስትና በወንጀል ሕግ አንቀፅ 197(2) መሰረት እንዲጠሩ ታዘዋል። በዚህም መሰረት ሁለተኛ ተከሳሽ ቀደም ሲል በዚህ መዝገብ ብር አንድ መቶ ለዋስትና ያስያዙ ስለሆነ ይሄው ለመተማመኛ ዋስትና እንዲውል ታዟል። ለፅህፈት ወጪ ሁለተኛ ተከሳሽ ብር 25.00(ሃያ አምስት ብር) እንዲከፍሉ ታዟል።

4 ኛ. የአዲስ አበባ ማረሚያ ቤት በአንደኛ ተከሳሽ ላይ የተወሰነውን የእስራት ቅጣት እንዲያስፈፅም ታዟል።

5 ኛ. ሁለተኛ ተከሳሽ ለፅህፈት ወጪ የተባለውንና የገንዘብ መቀጮውን ሲከፍሉ ይለቀቁ፤ አንደኛ ተከሳሽ ግን የእስራት ጊዜውን ሲጨርሱ ወይም በአመክሮ ሲፈቱ የገንዘብ መቀጮውን መክፈላቸው ተረጋግጦ እንዲለቀቁ ታዟል።
ይፃፍ።

6 ኛ. የይግባኝ መብት እንዳለ በችሎት ተነገረ።

7 ኛ. መዝገቡ ተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።